## ው ሣ ኔ

- የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.06203 በ10/10/96 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፤

መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡



የሰበር መ/ቁ. 17077

ጥቅምት 14 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጐስ ወልዱ

4. አቶ ዳኜ መላኩ

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች፡ - ዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል**

**መልስ ሰጪ፡ - አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ**

ውል፡ - ስለዋስትና - በዋናው ባለዕዳ ግዴታ ላይ ስለሚደረግ መለዋወጥ (ዋሱን ሣያስፈቅድ ባለገንዘቡ ለባለእዳው የመክፈያ ጊዜ የማራዘሙ ውጤት)፡ - የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1928(1)

አመልካች የእዳ መክፈያ ጊዜውን ዋስ የሆነውን መልስ ሰጭን ሳያስፈቅድ ያራዘመ በመሆኑ መልስ ሰጪ (ዋሱ) ከገባው ግዴታ ነፃ ነው በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

**ውሣኔ፡ - የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያፀናው ውሣኔ ተሽሯል፡፡**

1. የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1928 (2) ዓላማ ከውሉ መፈፀም በኋላ በባለገንዘቡና በባለእዳው መካከል የዋሱን ግዴታዎች የሚያባብሱ አዲስ ስምምነቶች እንዳይደረጉና ዋሱን ለተጨማሪ ጉዳት እንዳይዳርጉት ለመጠበቅ ነው፡፡
2. የመፈፀሚያ ጊዜ የተያዘላቸውና ዋስትና የተገባላቸው ግዴታዎች የግዴታ መፈፀሚያ ጊዜያቸው ሲጠናቀቅ ዋስ ላልተፈፀመው ግዴታ ተጠያቂ እንደሚሆን ሁሉ ከግዴታው መፈፀሚያ ጊዜ በኋላ ባለገንዘቡ በራሱ ፈቃድ በችሮታ መልክ የሚያደርገው የክፍያ ጊዜ ማሻሻያ ሆነ ሌሎች እርምጃዎች ዋስትና ከተገባለት ከቀድሞ ግዴታ ጋር የማይገናኝ በመሆኑ ለበሰለው እዳ ከመጠየቅ አይድንም፡፡



የሰበር መ/ቁ. 17077

ጥቅምት 14 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጐስ ወልዱ

4. አቶ ዳኜ መላኩ

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች፡** - ዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል - አቶ ፍቅሬ ሞያ ቀረቡ

**መልስ ሰጪ፡** - አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ - ጠበቃ መኰንን ሽፈራው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር ማመልከቻ መነሻ የሆነው ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቶች የአሁኑ አመልካች የእዳ መክፈያ ጊዜውን ዋስ የሆነውን የአሁኑን ተጠሪ ሳያስፈቅድ ያራዘመ በመሆኑ ዋሱ ከገባው ግዴታ ነጻ ነው ብለው ውሣኔ በማስተላለፋቸው ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ፣ ተጠሪ ስለደንበኛው በመሆን አውጥቼው ለበረው የብረት ግዢ ጨረታ የጨረታ ማስከበሪያ ቢድ ቦንድ አመልካችን ተጠቃሚ በማድረግ የሰጠ ስለሆነ የተጠሪ ደንበኛ የሆነው ድርጅት በጨረታ አሸናፊነቱ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና በ10 ቀናት በማቅረብ ውሉን እንዲፈርም ቢጠየቅ ይህን ባለመፈፀሙ የቢድ ቦንድ ዋጋውን ተጠሪ እንዲከፍለው ጠይቋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በበኩሉ የተለያዩ ነጥቦች ያካተተ መልስ የሰጠ ሲሆን በዋነኛነት ከሳች የተከሳሽ ደንበኛ ማሸነፉን ገልጾ ደብዳቤ ሲጽፍለት ከጨረታ ቅድመ ሁኔታና ከተከሣሽ ፈቃድ ውጭ የፊርማውን ቀን በ10 ቀናት አራዝሟል፡፡ በዚህም ሳያበቃ ለተጨማሪ 5 የሥራ ቀናት እንዲራዘም አድርጓል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ ያለተከሳሽ ፈቃድ የግዴታ ጊዜውን በማራዘሙ ከተጠያቂነት ነጻ ነኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍ/ቤትም አመልካች የተጠሪ ደንበኛ ጨረታ ያሸነፈ መሆኑን በመግለጽ ጥር 6 ቀን 1994 ዓ.ም. በቁጥር ዝስሮሚ/200/07/94 በተጻፈ ደብዳቤ ውሉን በመፈረም የመልካም ሥራ አፈጻጸሙን በአሥር ቀን ውስጥ እንዲያቀርብ፣ ይህ ሳይሆን ቀርቶ



ለማደርስ ጉዳት ተከሣሽ በገባው ግዴታ መሠረት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመግለጽ ለተከሣሽ ደንበኛ በጻፈው ደብዳቤ ገልጿል፡፡ የአሁኑ አመልካች በመቀጠል ጥር 21 ቀን 1994 ዓ.ም ቁጥር 2 ዩኤስኦ ኤም/200/05/94 በሆነ ደብዳቤ የተባለውን ጊዜ በ5 ቀናት ያራዘመ መሆኑን ለተከሣሽ ደንበኛ ገልጾ ጽፏል፡፡ እነዚህ ደብዳቤዎች የተጠሪ ደንበኛ ውል እንዲዋዋልና ዋስትናውን እንዲያቀርብ የተሰጠውን 10 ቀናት ያለ ዋሱ ፈቃድ ማራዘማቸውን የሚያስረዱ በመሆናቸው በሕ.ቁ.1928/2/ መሠረት ዋስ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ ከገባው ግዴታ ነጻ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ አመልካች ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ይግባኙ ውድቅ ሆኖ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡

አመልካች በሰበር እንዲታይለት ያቀረበው ማመልከቻ ይህንን ነጥብ የሚመለከት በመሆኑና የሕግ ትርጉም የሚያስነሳ ነጥብ ያለው መሆኑን በማመን ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጐ የተጠሪ መልስና የአመልካች የመልስ መልስ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ይህ የሰበር ችሎት ጉዳዩን መርምሯል። በዚህ ጉዳይ የሕግ ትርጉም የማያስፈልገው ነጥብ፣ በዋስትና ውል የተመለተን የአንድ ግዴታ መፈፀሚያ ጊዜ፣ የመፈፀሚያ ጊዜ ካበቃ በኋላ ባለገንዘቡ የዋሱን ፈቃድ ሳይጠይቅ በራሱ ችሮታ ተጨማሪ የማስፈፀሚያ ጊዜ ለባለዕዳው ሰጥቶ ቢገኝ ድርጊቱ ዋሱን ከተጠያቂነት ነፃ ያደርገዋል ወይስ አያደርገውም? የሚለው ይሆናል።

እንደሚታወቀው ለአንድ ግዴታ አፈጻጸም ዋስ የሚሆን ሰው ባለዕዳ እንዲፈጽም የሚጠየቀውን ግዴታ በተስማማበት ሁኔታ ወይም ጊዜ ያልፈፀመ እንደሆነ ይህንኑ ግዴታ ለባለገንዘቡ ለመፈፀም የሚገደድ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1920 ላይ ተደንግጓል። ግዴታውን እንዲፈጽም የሚጠራ ማንኛውም ዋስ ከውሉ መፈፀም በኋላ በባለገንዘቡና ባለዕዳው መካከል የእርሱን ግዴታዎች ያባባሱ አዲስ ስምምነቶችን በማንሳት ግዴታውን ላለመፈፀም መከራከሪያ ሊያደርጋቸው የሚችል መሆኑን ቁጥር 1928/1/ ያስገነዝባል። በዚህ አንቀጽ በተለይ በንዑስ ቁጥር 2 የዋሱ ፈቃድ ሳይኖር በባለገንዘቡ



የሚደረግ የመክፈያ ጊዜ ማራዘሚያ ተግባር ዋሱን ከነጭራሹ ከተጠያቂነት ነጻ የሚያደርገው መሆኑ ተመልክቷል።

በያዝነው ጉዳይ የተጠሪ ደንበኛ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትናውን እንዲያቀርብና ውል እንዲዋዋል አመልካች ደብዳቤ መጻፉ ተረጋግጧል። ዋሱን ጨምሮ ግዴታ የገቡበት የግዴታ መፈፀሚያው ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ደግሞ አመልካች ሌላ ተጨማሪ ቀናት የሰጠ ደብዳቤ መጻፉ ታውቋል። የአሁኑ ተጠሪ አመልካች በራሱ ፈቃድ ያደረገው የተጨማሪ ጊዜ ችሮታ የእኔን ዋስትና ቀሪ ያደርገዋል በማለት ተከራክሯል። በዚህ ደረጃ ትኩረት ተሰጥቶት በዋንኛነት ሊታይ የሚገባው ነጥብ፣ የአሁኑ አመልካች የግዴታ መፈፀሚያ ጊዜውን ካለዋሱ ፈቃድ አራዝሟል የተባለው መቼ ነው? የሚለው ይሆናል። ከጉዳዩ በግልጽ መረዳት እንደተቻለው የአሁኑ አመልካች ጥር 6 ቀን 1994 ዓ.ም የተጠሪ ደንበኛ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ የመልካም ሥራ አፈጻጸም እንዲያቀርብና ውል እንዲዋዋል ሲገለጽለት ይህ ሳይሆን ቀርቶ ለሚደርስ ጉዳት የአሁኑ ተጠሪ በገባው ግዴታ መሠረት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ገልጿል። ከሕጉና

ከዚህ ደብዳቤ መንፈስ መረዳት የሚቻለው ነገር ከተባለው 10ኛ ቀን በኋላ ማለትም ከግዴታው መፈፀሚያ ጊዜ ማብቂያ በኋላ ባለዕዳው የተመለከቱትን ግዴታዎች ፈጽሞ ካልተገኘ ዋሱ በባለዕዳው እግር ተተክቶ ግዴታውን መፈፀም እንደሚገባው ነው፡፡ በአንጻሩ ከዋሱ ፈቃድ ውጭ ከግዴታ መፈፀሚያ ማብቂያ ጊዜያት በፊት በዋናው ባለዕዳ ግዴታ ላይ የሚደረግ ለውጥ ዋሱን ነጻ የሚያወጣው መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1928/2/ ያስገነዝባል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ዓይነተኛ አላማ ከፍ ብለን ለመግለጽ እንደሞከርነው ከውሉ መፈፀም በኋላ በባለገንዘቡና ባለዕዳው መካከል የዋሱን ግዴታዎች የሚያባብሱ አዲስ ስምምነቶች እንዳይደረጉና ዋሱን ለተጨማሪ ጉዳት እንዳይዳርጉት ለመጠበቅ ነው፡፡

በዚህ መሠረት ጊዜ የተያዘላቸውና ዋስትና የተገባላቸው ግዴታዎች የግዴታ መፈፀማያ ጊዜያቸው ሲጠናቀቅ ዋስ ለግዴታው ተጠያቂ እንደሚሆን ሁሉ ከግዴታው መፈፀሚያ ጊዜ በኋላ ባለገንዘቡ በራሱ ፈቃድ በችሮታ መልክ የሚያደርገው የክፍያ ጊዜያት ማሻሻያም ሆነ ሌሎች እርምጃዎች ዋስትና ከተገባለት ከቀድሞ ግዴታ ጋር



የማይገናኝ በመሆኑ ለበሰለው እዳ ከመጠየቅ የሚያድን አይሆንም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ሕጉ ሊጠብቀው ከተነሳው ዓላማ በመውጣት የአሁኑ አመልካች የግዴታ መፈፀሚያ ጊዜው ያለፈበትን ግዴታ ከዋሱ ፈቃድ ውጪ አራዝሞአል በማለት ዋሱ ከተጠያቂነት ነጻ እንዲሆን የተከተለው አካሄድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሆኑም ግዴታ የተገባባቸው መፈፀሚያ ጊዜያት ከተጠናቀቁ በኋላ ባለገንዘቡ ለዋናው ባለዕዳ የሚሰጣቸው የችሮታ መፈፀሚያ ጊዜያትም ሆኑ ሌሎች እርምጃዎች ዋሱ ግዴታ የገባበትን የቀድሞውን ግዴታ መፈፀሚያ ጊዜያት ማራዘሚያ ተደርገው ሊወሰዱ አይገባም በማለት ይህን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ውሣኔ

- የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
- ተጠሪ በገባው ግዴታ መሠረት የቢድ ቦንድ ዋጋ ብር 239,600 (ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ብር) ይህ ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ለአመልካች ይከፈል፡፡

- የዳኝነቱን በታሪፉ መሠረት የጠበቃ አበል 10% ለአመልካች ይክፈል
- መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡



የሰበር መ/ቁ. 17189

ጥቅምት 17 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

4. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች፡** - የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት

**መልስ ሰጪ፡** - አቶ ንጉሴ ዘለቀ

*የስራ ግንኙነትን ስለማቋረጥ - በአሰሪ አነሳሽነት የሚደረግ የስራ ውል መቋረጥ - ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ስለማቋረጥ - ስለ ደመወዝ - ስራ ላልተሰራበት ጊዜ ክፍያ ስለሚደረግበት ሁኔታ፡ -*

የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 27/1/በ፣ 53/1/፣54 መልስ ሰጪ የአመልካች ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ሆኖ በማሰራበት ወቅት በስሩ የሚገኘውን ገንዘብ ያኘ በተገቢው ሁኔታ ባለመቆጣጠሩ የአሰሪው ድርጅት ገንዘብ እንዲመዘበር ምክንያት በመሆኑ መ/ሰጪ ከስራ የተሰናበተው በአዋጁ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27(1) (በ) መሠረት በአግባቡ ነው በሚል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር